ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፩

❊❊❊

ጥያቄ ፦ ፍልስፍና ምንድን ነው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ " ፍልስፍና ምንድነው የሚለው? " የሚለው ጥያቄ ራሱ የፍልስፍና ጥያቄ ነው ።

ለሌሎች የትምህርት ዘርፎች ማለትም ለእነ ሳይንስ ፣ ለእነ ታሪክ ፣ ለጥናት ማዕከሎች መነሻ የሚሆኑት ጉዳዮችና የፍልስፍና ጉዳይ ይለያያል ። "ሳይንስ ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ ለሳይንስ ተቀዳሚ ጥያቄ አይደለም ። "ታሪክ ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ ለታሪክ ተቀዳሚ ጥያቄ አይደለም ። ፍልስፍና ግን በአንፃሩ የራሱን ምንነት ማዕከላዊ አድርጎ የሚንቀሳቀስ የትምህርት ዘርፍ ነው ። የሂሳብ ሰዎች "ንተሃ" ብለው ሲነጋገሩ ፈላስፋ ቢመጣ " ለመሆኑ ቁጥር ምንድን ነው? " ብሎ ነው የሚጠይቀው ። ሠዓሊያን ስለቀለሙ ፣ ስለ ሥዕሉ ፣ ስለ ቅርጹ ሲያወሩ ቢሰማ "ለመሆኑ ሥዕል ምንድነው?" ነው የሚለው ።

⁞

ሌሎች የትምህርት ዘርፎች ለምሳሌ የሂሳብ ባለሙያና ሠዓሊው ቁጥርንና ሥዕልን እንዳሉ አድርገው ተቀብለው ወደ ተግባር ሲሄዱ ፈላስፋው ግን በሁለቱ ሙያዎች መሀል ያለውን መሠረታዊ ምንነት በመመርመር ይጀምራል ። ፍልስፍና ይበልጡን ጥያቄ ላይ ያተኩራል ። ለፍልስፍና ጥያቄው የመልሱን ያህል ዋጋ ያለው ነው ። በመሆኑም በማንኛውም መልኩ ሕይወትን በሚመለከት ዘለቄታዊና ትልቅ ጥያቄ እያነሳ ትልልቅ መልሶችን ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ ነው ።

⁞

ጥያቄ ፦ ከጥያቄውና ከመልሱ ለፍልስፍና የቱ ይቀርባል?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ ጥያቄው ። እንደውም ፍልስፍና የጥያቄ ሳይንስ ነው ሊባል ይችላል ። የተወሰኑ ድባቦችን ፣ አድማሶችን ፣ የቱንም ጉዳይ ፣ የቆምክበትን ሃሳብ ሁሉ እንድትጠይቅ ነው የሚያደርግህ ። ሁሉም መልስና ውጤት ሊገኝ የቻለው በመጀመርያ ጥያቄ ማንሳት ሥለተቻለ ነው ። ለዚህም ነው በፍልስፍና ጥያቄው የመልሱን ያህል ዋጋ አለው መባሉ ።

⁞

ጥያቄ ፦ ወይም ደግሞ በሌላ አነጋገር ፍልስፍና ጠይቆ መልስ ማግኘት ሳይሆን መልሱን መጠየቅ ነው ልንለው እንችላለን?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ በትክክል እንችላለን ። ፍልስፍ "አለቀ ፣ በቃ" የሚባል መልስ የለውም ። መልሱንም ይጠይቃል ። ራሱ የጠየቀውንም የሚጠይቅ ነው ። ፍልስፍና የማይወዳቸው አንድ ፣ ሁለት ፣ ሶስት ነገሮች አሉት ። እንደውም ጠላቱ በላቸው ።

⁞

ጥያቄ ፦ ሦስቱ የፍልስፍና ጠላቶች ምንድንናቸው?

ይቀጥላል...

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፪

❊❊❊

ጥያቄ ፦ሦስቱ የፍልስፍና ጠላቶች ምንድን ናቸው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ አንደኛው #እርግጠኝነት ነው ። እርግጠኝነት ወደ ዶግማ፣ ቀኖና ይወስዳል ። በትራንድ ራስል እንደሚለው ፍልስፍና ያነሳቸው ጥያቄዎች እርግጠኛ መልስ ከተገኘላቸው ፍልስፍና መሆኑ ይቀርና ሌላ ዘርፍ ውስጥ ይገባል ። እርግጠኛ ካለመሆን የሚንቀሳቀስ የእውቀት ዘርፍ ነው ፍልስፍና ። ራስል እንደገና ምን ይላል መሰለህ? "ፍልስፍና እርግጠኛ ወደአለመሆን ስለሚወስድህ ከባህል ከሚነሳው እስረኝነት ነፃ ሊያወጣህ ይችላል ። ይኸውም የሚሆነው የሚሆነው የእርግጠኝነትን ሰንሰለት ሰብሮ ስለሚሔድ ነው" ይላል ። በመሆኑም እርግጠኝነትን ፍልስፍና አይወደውም ። እርግጠኝነት በጣም ችግር አለው ።

⁞

ፍልስፍና ከማይወዳቸው መሀል ሁለተኛው #በጋራ_መግባባት ነው ። በአንድ ጉዳይ ላይ ብዙዎች በጋራ ተስማሙ ወይም አንዱ ሳይስማማ ቀረ ጉዳዩ አይደለም ። በመጀመርያ ደረጃ ፍልስፍና የጋራ መስማማት (የጅምላ አንድነት) ላይ አይስማማም ። ቀጥሎም ለፍልስፍና ትልቁ ጉዳይ ቁጥር ሳይሆን ምክንያታዊነት ነው ።

⁞

ሦስተኛው ነጥብ "ይህ ነው" ብለህ ከቀን ከቀን ሕይወትህ የምታየውን ነገር ዞር አድርጎ ከተለየ አቅጣጫ እንድታየው ማድረጉ ነው ። አንድ ጊዜ "ልክ ነው" ብለው የተቀበሉትን እውነት እንደገና ሳይፈትሹና ሳይመረምሩ እንደተቀበሉ መቅረትን ፍልስፍና አይወደውም ። እንደ ፕሌቶ አስተምህሮት የምናየውን ነገር በሌላ አቅጣጫ እንድናይ ፣ የምንሰማውን በሌላ አቅጣጫ እንደገና እንድንሰማ ፣ ከተቀባይነት አልፈን ጥያቄ እንድናነሳ የሚያስችለን ነው ። ይህንንም ፕሌቶ *metastrophy* ይለዋል ። ፍልስፍና ከዚህ በፊት ያልተጠየቁ እውነታዎችን እንድንፈትሽ የሚያደርገን መሳርያ ነው ።

⁞

ጥያቄ ፦ በፍልስፍና ውስጥ መልስ የሚባል ውጤት የለም እያልን ነው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ አለ ። መልስ አለ ። ግን እርግጠኛ የሆነ መልስ ሲኖር ወደ ሌላ መንገድ ይወስዳል ብሎ ያምናል ፍልስፍና ። እነ ሳይንስ ለእርግጠኝነት የሚሔዱ ናቸው ። ፍልስፍና ግን የመጠየቅና ጥያቄውን ከነመልሱ የመመርመር ጥበብ ነው ።

⁞

ጥያቄ ፦ ፍልስፍና ለሰው ልጆች ምን ሰጠ?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ እጅግ ብዙ ነገር ሰጥቷል ። ፍልስፍና ለሰው ልጅ የአኗኗር ዘዴ፣ ለፖለቲካው ስርአት በርከት ያሉ አስተዋፅኦዎችን አድርጓል ። የእነ አሜሪካና ፈረንሳይ ህገ መንግስቶች የታሰቡትም ሆነ የተፀነሱት በፈላስፎች ነው ። ፈላስፎቹ በየዘመኑ ባነሱት ጥያቄ ነው ሀገራት እዚህ የደረሱት ።

⁞

ጥያቄ ፦ ፍልስፍና በቅድመ መነሻነት ለመፈጠሩ ምክንያቱ ምንድነው?

ይቀጥላል...

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፫

❊❊❊

ጥያቄ ፦ ፍልስፍና በቅድመ መነሻነት ለመፈጠሩ ምክንያቱ ምንድነው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ ይህ ጥያቄ የጥበባት ምንጭ ወደሆነችው ግሪክ ነው የሚወስደን ። ግሪኮች ፍልስፍናን ወይም እውቀትን መውደድ (*love of wisdom*) እንዴት ጀመሩ የሚለው ጥያቄ ወደ መልሱ ያመራናል ። የሄለና ስልጣኔ በንግድና የተለያዩ የእውቀት ዘርፎች ያደገ ከመሆኑም በላይ ትላልቅ ሀሳቦች የተነሱበትም ጭምር ነው ። ፍልስፍና ከመጀመሩ በፊት በግሪክ ስልጣኔ ውስጥ ወሳኝ ድርሻ የነበራቸው ባለቅኔዎች (*poets*) ነበሩ ። እነ ሆሜርና ሂሶይድን የመሳሰሉት ባለቅኔዎች የታሪክ መዝጋቢ ፣ የስነ ምግባር ምግባር አስተምህሮት አቅራቢና የፖለቲካ ተንታኞችም ነበሩ ። በሀገሪቱ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ጭቅጭቅ ሲነሳ "ሆሜር ምን አለ?" ነው የሚባለው ።

⁞

እነዚህ ባለቅኔዎች ከስነምግባር አስተምህሮት አቅራቢነታቸው ፣ ከታሪክ አዋቂነታቸውና ፖለቲካ ተንታኝነታቸው በዋናነት በሁለት ነገሮች ላይ የበላይነት ነበራቸው ። አንዱ ኃይማኖታዊ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በስርዓት ስለምትመራው ዓለም (*cosmos*) የሚተነትኑ ናቸው ። ኃይማኖቱን በሚመለከት አማልክቱን (*mythology*) ስያሜና ገፀባህሪ የፈጠረው ሆሜር ነው ። "ዙስ እንዲህ ነበር፤ አቴና እንዲህ ናት፤ ፖሳይደን..." እያለ ሥራ ያከፋፈላቸው ሆሜር ነው ። ስለ ምድረ ዓለም (*cosmos*) አፈጣጠርና ሁኔታ የሚያወሩትም እነዚሁ ባላቅኔዎች ናቸው ። በአጠቃላይ እነዚህ ባለቅኔዎች በግሪክ የባህል፣ የአዕምሮ፣ የአስተሳሰብ ዘይቤ ላይ የበላይነት ነበራቸው ።

⁞

በሂደት ግን አዲስ አይነት አሳቢዎች ተፈጠሩ ። አዲሶቹ ሰዎች እነ ሆሜርን በድፍረት "እናንተ ብቻ አይደላችሁም ስለ

አማልክቱ የምታውቁት ። ስለ አማልክቱ የምታወሩትም በእግሩ የሚቆም አይደለም" አሏቸው ። ለምሳሌ ከነሶቅራጥስ በፊት የመጣው ዜኖፊነስ ካቀረባቸው ትችቶች መሀል በዋናነት የሚጠቀሰው ባለቅኔዎቹ ስለ አማልክቱ ያላቸው አቀራረብ ላይ ጥያቄ አንስቷል ። በእሱ አስተያየት የባለቅኔዎቹ ችግር በራሳቸው አስተያየት እግዚአብሔርን መቅረፃቸው ላይ ነው ። "Anthropomorphism" ነው የተቸው ። " በራሳችሁ ምስል እግዚአብሔርን ትቀርፃላችሁ " ነው ያላቸው ።

⁞

አማልክቱን በሚመለከት ባለቅኔዎቹ ላይ የመጀመርያውን ሂስ ያካሔዱት እነ ዜኖፊነስ ናቸው ። በሁለተኛ ደረጃ የነበራቸው ጠብ ፍጥረትን በሚመለከት ነው ። ለምሳሌ አናይዛጎረስ የተባለው ፈላስፋ ባለቅኔዎቹ እነሆሜርና ሂሶይድ "ጨረቃ መለኮታዊ ስሪት ናት" ያሉትን ሲተች "ጨረቃ እናንተ እንደምትሉት መለኮታዊ ነገር አይደለችም ። ምንም የተለየ ክብር አይገባትም ። ፕላኔት ላይ የተንጠለጠለች የሞቀ ድንጋይ ናት" ነው የሚለው ።

⁞

ፈላስፎቹ መጥተው የድንጋዩን፣ የጨረቃንና የተራራውን መለኮታዊ ክብር ገፈው ግዑዝ ፍጥረት አደረጓቸው ። እንግዲህ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በባለቅኔዎቹና አዲስ አይነት አስተሳሰብ ይዘው በቀረቡት መሀል የነበረው ግጭት በአማልክቱ አገላለፅና በምድራዊው አለም አፈጣጠር ዙርያ ረዘም ያለ የአመለካከት ግጭት አካሂዷል ። እንግዲህ ፍልስፍና የተፈጠረው ፈላስፎቹና ባለቅኔዎቹ በኃይማኖትና በምድራዊው ዓለም ዙርያ ባደረጉት ፍልሚያ ነው ማለት ነው ።

⁞

ጥያቄ ፦ ኃይማኖት ምንድን ነው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ኃይማኖት(Religion) የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርገው ጉዞ ነው ። Revelation ደግሞ እግዚአብሔር ሰውን ለማግኘት(ወደ ሰው) የመጣበት ጉዞ ነው ። እንግዲህ ኃይማኖት ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበትን መንገድ ያስተምራል ። ከእግዚአብሔር ቃል በመነሳት በጎነትን፣ የሞራል ሰናይነትን፣ መልካምነትን ወዘተ ያስተምራል ። የሰውን ባህሪና ፀባይ አርቆ ሰውን ሰው ለማድረግ ኃይማኖት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል ።

⁞

ጥያቄ ፦ ሁለቱ(ፍልስፍናና ኃይማኖት) ተቀራራቢ ወይስ ተገፋፊ ኃይሎች ናቸው?

ይቀጥላል...

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፬

⁂

ጥያቄ ፦ ሁለቱ(ፍልስፍናና ኃይማኖት) ተቀራራቢ ወይስ ተገፋፊ ኃይሎች ናቸው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ በዚህ ጥያቄ ዙርያ የላቀ ጥናት ያቀረቡት የ፲0ኛው ክ/ዘመን እውቁ አሜሪካዊ ፈላስፋ ፕሮፌሰር ሊዎ ስትራውስ እንዳሉት "ኃይማኖትና ፍልስፍና ሊዋሀዱ አይችሉም ። ነገር ግን ሁለቱም ዘርፎች በመቻቻል እንዲኖሩ ከተደረገ አንዱ ለሌላው አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል ። በመሆኑም ምክንያታዊነት ከኃይማኖት የመነጨ የሞራል አስተምህሮት ካልታከለበት ወደ ስታሊን ጉላግና የሂትለር Concentration Camp ይወስደናል ። በሌላ በኩል ደግሞ ኃይማኖትም የምክንያታዊነት ግብአት ከሌላት ወደ አክራሪነትና Spanish Inquisition ይወስዳል በመሆኑም በታሪክ እንዳየነው ሁለቱን አቻችለው መሔድ የቻሉ ስልጣኔዎች ትልቅ ቦታ መድረስ ችለዋል ።

⁞

ጥያቄ ፦ እነዚህ ሁለቱ የእምነትና የምክንያታዊነት አድማሶች የሚገዙላቸው እውነቶች ምንድናቸው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ የኃይማኖት እውነት ከእግዚአብሔር በተገለፀ እውነታ(Revelation) ላይ የተመሠረተ ነው ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ እምነት ነው እውነቱ ። በሌላ በኩል ደግሞ የፍልስፍና እውነት በምክንያታዊነት ላይ የተመረኮዘ ነው ። ኃይማኖትና ፍልስፍናን ስናነፃፅር ኃይማኖት "ለማመን ከፈለክ ተቀበል" የሚል መርህ ሲኖረው ፍልስፍና ደግሞ "ቃሉን መርምረህ ተቀበል" ነው የሚለው ። ፍልስፍና ሃላፊነቱን ሰው ልጅ ትጋት ላይ ይጥላል ። ኃይማኖት ላይ ሰው ተቀባይ(passive) ሲሆን ፍልስፍና ግን መርማሪ(Active) ነው ። ለምሳሌ ሁለቱን የቃል (logos) አስተማሪዎች ብንወስድ ክርስቶስ "እኔ እውነትና መንገድ ነኝ" ብሎ እንድትቀበለው ሲነግርህ ከክርስቶስ ልደት 500 ዓመት በፊት የነበረው ትልቁ ፈላስፋ ሄሬክላይተስ ደግሞ "እኔን አትስሙ፤ ቃሉን ግን ስሙ" ነው ያለው ። እንግዲህ ቃልን(logos) በሚመለከት የሁለቱ አመለካከት የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን ። የመጀመርያው (ቃሉን ተቀበል) ኃይማኖታዊ ሲሆን (ቃሉን መርምር) ፍልስፍናዊ ነው ።

⁞

ጥያቄ ፦ የፍልስፍናና የኃይማኖት ሰዎች የሚጋጩበት ምክንያት የቅርጽ ብቻ ሳይሆን የይዘትም ልዩነት ያለው ነው ። በአተገባበር ሳይሆን በዋንኛነት በአምልክ መኖርና አለመኖር ላይም መሰረታዊ ልዩነት ያመጣሉ ። እነዚህ ግጭቶች መሀል ያለው የሀሳብ ልዩነት ምን መልክ አለው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ እንግዲህ ፍልስፍና የተፈጠረው በኃይማኖት ዙርያ በተነሳ አለመግባባት መንስኤነት ነው ብለናል ቀደም ሲል ። በአምላክ መኖርና አለመኖር ዙርያ ለዘመናት ልዩነቶችና ግጭቶች ተነስተዋል ። ፍልስፍና ከኃይማኖት ተፃራሪ ሆና የቆየችባቸው አመታት እንዳሉ ሁሉ ፍልስፍና የኃይማኖት አገልጋይ እንትሆን የተደረገባቸው አመታትም ነበሩ ። በእነዚህ አለመግባባቶች ከውይይትና ክርክሮች እስከ ሕይወት መስዋዕትነት እንደተከፈለበት ታሪክ ይነግረናል ።

⁞

ጥያቄ ፦ "አምላክ የለም" ብለው የሚከራከሩ ወገኖች ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ደጋግመው የሚያነሱት ዓለማችን ባለቤት የለሽ እስክትመስል ድረስ የሚታይባት የፍትህ እጦት፣ የንፁሀን ስቃይና ሰናዮች ያለጥፋታቸው መቀጣት ነው ። የሰው ልጅ ያለጥፋቱ የሚወርድበት መከራና ስቃይ አምላህን ፍትህ የለሽ ከማድረጉም በላይ "ቢኖር ይህ አይሆንም፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አምላክ የለም" እንዲሉ አድርጎቸዋል ። ፍልስፍና ይህን እንዴት ያየዋል?

ይቀጥላል...

ክፍል ፭ ቶሎ ይቀጥል ዘንብ አብሮነታችሁን አሳዩን...

@filsfina @filsfina

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፭

⁂

ጥያቄ ፦ "አምላክ የለም" ብለው የሚከራከሩ ወገኖች ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ደጋግመው የሚያነሱት ዓለማችን ባለቤት የለሽ እስክትመስል ድረስ የሚታይባት የፍትህ እጦት፣ የንፁሀን ስቃይና ሰናዮች ያለጥፋታቸው መቀጣት ነው ። የሰው ልጅ ያለጥፋቱ የሚወርድበት መከራና ስቃይ አምላህን ፍትህ የለሽ ከማድረጉም በላይ "ቢኖር ይህ አይሆንም፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አምላክ የለም" እንዲሉ አድርጎቸዋል ። ፍልስፍና ይህን እንዴት ያየዋል?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ ይህም ጉዳይ ለአመታት አወያይቷል ። "The problem of evil" ይሉታል ። በዚህ ጥያቄ ዙርያ ሁለት ታላላቅ ፈላስፋዎችን እንጠቅሳለን ። አንዱ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፭፻፷-፭፸፬ ዓ.ዓ የኖረው ኤፒኪረየስ ሲሆን ሌላው ደግሞ ቅዱስ ኦገስቲን(፫፭፭-፬፯፩ ዓ.ም) ነው ። ኤፒኬሪያስ ይህን ጉዳይ ሲገልፅ "አምላክ እርኩሰትን ለማስቆም ፍላጎት እይለው ካልቻለ አቅም የለውም ማለት ነው ። አቅሙ ኖሮት ፍቃዱ ካልሆነ ደግሞ በጎ አይደለም ማለት ነው ። አቅሙም ፍላጎቱም ካለው ታዲያ እርኩሰት ከየት መጣ? ብሎ ጠይቋል ።

⁞

በ፲፯ኛው ክ/ዘመን ራሽያዊ የረጅም ልቦለድ ፀሐፊ ፊዮዶር ዶስቶዮቪስኪ "የካራማዞቭ ወንድማማቾች" በሚለው መጽሐፉ ላይ ሁለቱ ወንድማማቾች ኢቫንና ኢሊዮሻ ሲወያዩ ፈላስፋው ኢቫን ለኃይማኖተኛው አሊዮሻ የሚከተለውን ጥያቄ ያነሳል ፦

" ትልልቅ ሰዎች ስቃይ ቢደርስባቸው ይገባኛል ። ንፁሀን፣ በተለይ ህፃናትን የረሀብ፣ የበሽታ፣ የጦርነት ሰቆቃ ለምን ይደርስባቸዋል? ለእንደዚህ አይነት ወንጀል ምንም አይነት ምክንያት ሊቀርብ አይችልም ። ንፁሀኑን በሚመለከት እግዚአብሔር ያሻውን ለማድረግ የመግቢያ ትኬት የለውም "

⁞

ጥያቄው ለሶሻሊስቶቹ ብቻ ሳይሆን ለትልቁ መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ አማኝ ዶስቶቪስኪም አሳሳቢና አስቸጋሪ ጥያቄ እንደሆነበት እንረዳለን ። ይኸው ጥያቄ በሀገራችን ገጣሚ ሙሉጌታ ተስፋዬም "እውነት ከመንበርህ የለህማ!" በሚል ርዕስ ተገልፆ እናያለን ፦

"... ግን፦ ግን...ብላቴናዎቹ ምን በደሉ?

የማንን አደራ በልተው...የማንን አማና አጎደሉ?

እምብርታቸው ያላረረ...አጥንታቸው ያልከረረ

ሰማይ በቀል እንደቋጠረ...እጣቸውን እየመነጠረ

መንገዳቸውን እያጠረ

እንደ ደራሽ ውሃ አግተልትሎ

በራብ አኮርማጅ ተልትሎ

ከእናት እቅፍ በግፍ ነጥቆ

ምሱን ሊቃመስ ተባጥቆ

ሲሰለፍብን ባጭር ታጥቆ

እያየህ ዝም ካልክማ...?

እውነት...እውነት ከመንበርህ የለህማ!... "

⁞

በevil ዙርያ ለተነሳው ጥያቄ ከቅዱስ ኦገስቲን ጀምሮ እስካሁን ድረስ "The free will defense" በሚባል ስያሜ የቀረበውን ወሳኝ የሆነ መልስ እናገኛለን ። ከቅዱስ ኦገስቲን በኋላ የመጡት ታላላቅ አማኝ ፈላስፋዎች እንደሚሉት "እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ነፃ ፍቃድ ሰጥቶታል ። ስለሆነም በጎውንም ሆነ ክፉውን የምንመርጥ እኛ ነን ። እግዚአብሔር ነፃ ፈቃድ ስለሰጠን ማመስገን እንጂ ማማረር የለብንም" በማለት ለበጎውም ሆነ ለevil የሰውን ልጅ ተጠያቂ ያደርጋሉ ።

⁝

ቅዱስ ኦገስቲን ሀሳባቸውን ሲገልፁም የሰው ልጅ በመጀመርያ ሲፈጠር መጽሐፉ እንደሚያስረዳው ጥሩ፣ ሀጢአትና ችግር የሌለበት ስፍራ ላይ ነው የነበረው ። ነፃ ፍቃዱን በአግባቡ ባለመጠቀሙ የተነሳ ችግር ወዳለበት ዓለም በሽረትና በቅጣት መጥቷል ብለው ይገልፃሉ

⁝

ጥያቄ ፦ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን መኖር በምክንያታዊነት ለማቅረብ የተደረጉ ጥናቶች አሉ ?

ይቀጥላል...

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፮

❊❊❊

ጥያቄ ፦ በፍልስፍና ታሪክ ወስጥ የእግዚአብሔርን መኖር በምክንያታዊነት ለማቅረብ የተደረጉ ጥናቶች አሉ?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ አዎን አሉ ። እነዚህ የእግዚአብሔርን መኖር ሊያስረዱ ይችላሉ የተባሉት ምክንያቶች በሦስት ዋና ዋና ዘርፎች የተከፈሉ ናቸው ።

እነሱም

1. Cosmological Argument

2. Teleological Argument

3. Ontological Argument ናቸው ።

⁞

Cosmological Argument ከተፈጠረው ነገር ተነስተን ለፈጣሪው እውቂያ የምንሰጥበት የአመለካከት ዘይቤ ነው ። ከዚህ በሚያያዝም ተፈጣሪ ወይም ኃላፊና ጠፊ (Contingent) የሆነ ነገር ሁሉ የማያልፍና የማይጠፋ አካል እንደፈጠረው ይገልፃል ። በዚህ የአመለካከት ዘይቤ ላይ "አምስቱ መንገዶች" ብለው ወሳኝ የሆነውን ድርሳን የፃፉት ቶማስ አኳይነስ (1225-1274) ናቸው ። እሳቸው እንደሚሉት...

"ያለ ነገር ሁሉ ለመኖሩ መንስኤ አለው ። ይህ ማለት ምንም ነገር የራሱ መንስኤ ሊሆን አይችልም ። በመሆኑም አንድ ሳይፈጠር ፣ የሚፈጥር ሳይንቀሳቀስ የሁሉም አንቀሳቃሽ የሆነ፣ በአጠቃላይ የሁሉም ነገር ፈጣሪና ምክንያት አለ ማለት እንችላለን" ይህንንም ሲሉ ቅዱስ አኳይነስ እግዚአብሔርን ማለታቸው ነው ።

በሌላ በኩል Cosmological Argument ሊመልስ የሚሞክራቸው ጥያቄዎች ለምንድነው ይህቺ ዓለም ያለችው? ለምንድነው አንድ ነገር ያለው? ለምንድነው ምንም (nothingness) የሌለው? ምንድነው እዚህ የምናደርገው? እነዚህን ወሳኝ ጥያቄዎች ለመመለስ ነው "እግዚአብሔር አለ" በሚለው መንገድ የምንሔደው ።

⁞

Telological Argument ይህቺ በስርዓት የምትመራ ዓለም ስናያት የማይዛባ ስርዓት ያላት ናት ። ቴክኖሎጂ የፈጠረውን ቁሳዊ ነገር (ስልክ፣ መኪና፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ) ስናይ እነሱን የፈጠራቸው አዕምሮ እንዳለ እንገነዘባለን ። በመሆኑም ለእነዚህ ቁሳዊ ነገሮች ፈጣሪ አላቸው እንዳልን ለዚህች ስርዓት ይዛ ለምትንቀሳቀሰው ዓለምና ለሰው ልጅ ፈጣሪ አለ ብሎ ከማሰብ ውጪ አማራጭ እንደሌለ የሚገልፅ የአስተሳሰብ ዘይቤ ነው ።

ሆኖም ግን የ19ኛው ክ/ዘመን የሥነ ተፈጥሮ ተመራማሪ ቻርልስ ዳርዊን "Origen of the Species" (1859) የተባለው ጽሑፉ ላይ ይህን Teleological Argument የሚፃረር ተቀናቃኝ አመለካከት አቅርቧል ። እንደ ዳርዊን

አቀራረብ የዚህች ዓለም ስርዓት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ሳይሆን በውስጧ በሚካሄደው ተፈጥሯዊ የመፈላለግና የመመራረጥ ሂደት (Natural selection) ላይ የተመረኮዘ ነው ።

⁝

Ontological Argument የዚክ ክርክር አባት ቅዱስ አንሰለም (1033-1109 ዓ.ም) ናቸው ። ይህ አቀራረብ የእግዚአብሔርን ምንነትና ትርጉም ይዞ ነው የሚነሳው ። ማለትም የእግዚአብሔርን ስያሜ ባነሳን ቁጥር የሚመጣልን ነገር ከርሱ በላይ ትልቅ የሆነ፣ በአዕምሯችን ልንገነዘበው የማንችለው ነው እንላለን ። "the greatest concevable being" እንላለን ። ሌላው ነገር እያለ እንዴት ትልቅና ውሱንነት የሌለው እግዚአብሔር ህልውና (existence) ሊያጣ ይችላል? ብለው ይጠይቃሉ ።

እነዚህ ታላላቅ መንፈሳዊ ሊቃውንት የእግዚአብሔርን መኖር በአመንክዮ ለማሳየት የሞከሩት እነሱ ራሳቸው ካቀረቡት ምክንያታዊነት ተነስተው ወደ እግዚአብሔር ለመሔድ ሳይሆን መኖሩን ከተቀበሉ በኋላ ለሌላው ለማሳወቅ ያደረጉት ሙከራ ነው ።

⁝

ጥያቄ ፦ እንደተገለፀው በየዘመናቱ ለእግዚአብሔር መኖርም ሆነ አለመኖር የሚደረጉ ጥናቶችና መኖሩንም ሆነ አለመኖሩን በምክንያት ለማስደገፍ የተደረጉ አዝማሚያዎች አሉ ። በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ባሉ ፈላስፎች ከአምላክ መኖርና አለመኖር ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ ያለው ሀሳብ የቱ ነው?

ይቀጥላል...

በቀጣይ ክፍል ፮ እና የመጨረሻውን ክፍል ይዘንላችሁ እንቀርባለን በንባብ እየተከተሉን ነው? እንግዲያውስ (

እየቀረበ ያለው ጽሑፍ ላይ ያላችሁን ማንኛውም አስታየት ካላችሁ @simba23 ላይ ላኩልን ።

@filsfina @filsfina

ፍልስፍና ምንድን ነው?

በሚሉ እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የምሁራን ትንታኔ

ክፍል ፮

(የመጨረሻው ክፍል)

⋮

ጥያቄ ፦ እንደተገለፀው በየዘመናቱ ለእግዚአብሔር መኖርም ሆነ አለመኖር የሚደረጉ ጥናቶችና መኖሩንም ሆነ አለመኖሩን በምክንያት ለማስደገፍ የተደረጉ አዝማሚያዎች አሉ ። በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ባሉ ፈላስፎች ከአምላክ መኖርና አለመኖር ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ ያለው ሀሳብ የቱ ነው?

ዶከተር ዳኛቸው ፦ በ፲፯ኛው ክ/ዘመን ላይ እግዚአብሔር አለ ብሎ ማመን ከኋላ ቀርነት የተቆጠረበት ጊዜ ነበር ። ለምሳሌ እነ ካርል ማርክስን የመሳሰሉ ፈላስፎች "እግዚአብሔር አለ" የሚለውን አስተሳሰብ የሰው ልጅ በእውቀት ያልተመራ ሃሳብ ውጤት እንደሆነ ሲገልጹ ተስተውለዋል ። ካርል ማርክስ ይህን ሀሳብ ሲያብራራ " እግዚአብሔርን የፈጠረው ሰው ነው ። እኛው ከፈጠርነው በኋላ የበላያችን አድርገን አነገስነው " ብሏል ። አሁን በአሜሪካና በእውሮፓ የኃይማኖት ፍልስፍና ዙርያ እጅግ በሚደንቅ መልኩ ክርክር እየተካሄደ ነው ።

⋮

በዚህ ወቅት ባለው ሁኔታ "እግዚአብሔር አለ" የሚል አቋም ያላቸው ፈላስፎች "የለም" የሚሉትን ፯ለ፣ እየመሯቸው ነው ። ቁጥር ብቻ ሳይሆን ቁጥር ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለመኖሩ የሚቀርበው የፍልስፍና ክርክር በእጅጉ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል ። በ፲፯ኛው መቶ ክ/ዘመን እግዚአብሔር የሚለው አስተሳሰብ የኋላ ቀርነት ምልክት የሆነውን ያህል በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተገላቢጦሽ "የለም" የሚሉት ላለመኖሩ ማሳመን እያቃታቸው ነው ። የምነግርህ የቁጥሩን መብዛት ብቻ አይደለም ። እንደውም ፍልስፍና በቁጥር አያምንም በምክንያታዊነት እንጂ ።

⋮

ጥያቄ ፦ እነዚህ ያነሳሳናቸው ጥያቄዎች ከዘመናት በፊት የተጠየቁ፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ያሉና ወደፊትም የሚጠየቁ ናቸው ። ያም ሆኖ ወሳኝ መልስ ያላቸው አይመስሉም ። ስለዚህ ጫፍ ጋር የማይደርሱበትን ጥያቄን የማንሳት ፋይዳ ምንድነው?

ዶክተር ዳኛቸው ፦ በፍልስፍና ዓለም *perennial* የሚባሉ በየትውልዱ ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ ። እነዚህም ጥያቄዎች በአጠቃላይ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር የተቆራኙ ጥያቄዎች ናቸው ። ለምሳሌ የኑሮ ትርጉሙ ምንድነው? ከየት መጣሁ? ለምን አሁን እዚህ አለሁ? ከዚህ ዓለም ከተለየን በኋላ ሌላ ሕይወት አለ? ይህች ዓለም የላቀ አዕምሮ የፈጠራት ናት ወይስ በአጋጣሚ የተፈጠረች? ሰው ላቅ ያለ አዕምሮ ያለው እንስሳ ነው ወይስ መለኮታዊ ባህሪ አለው?...የሚሉትን አይነት ጥያቄዎች በማንሳት እውነቱን መጨበቅ ባንችልም ያለንበትን ለመረዳት የተወሰነ *wisdom* እንድናገኝ ይረዳናል ። በተጨማሪም እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎችን የተለያዩ ትውልዶች እያነሱ በመፈተሽ የየራሳቸውን መልስና ትንታኔ ለመስጠት መሞከር ይኖርባቸዋል ። የሰው ልጅ አልፎ አልፎ ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎችን በማንሳቱ የአዕምሮና የሞራል ክብረት ይጎናፀፋል ተብሎ ይታመናል ። ስለዚህ የጥያቄዎቹ መነሳት ተገቢነት ያለው ከመሆኑም ባሻገር መቀጠል ያለበትም ነው ።

※ ተፈፀመ ※

ምንጭ ፦ ፍልስምና ፬ + ፪ + ፫

ደራሲ ፦ ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ

ሕትመት ፦ ሐምሌ ፪010

ከፍልስፍና ዓለም እንዲሁም ንባብ ለሕይወት የቴሌግራም ቻናሎች ዝግጅት ክፍል

@filsfina @filsfina

@booksforall32 @booksforall32